የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፺፫
አዲስ አበባ ጥር 29 ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33th Year No.93
Addis Ababa 6th day, feb, 2025

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፻፹፫/፪ሺ፲፮**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብስክሌት መጋራት አገልግሎት እና የብስክሌት መስመር አጠቃቀም ደንብ**

**ገፅ**……………………………………………፫ሺ፰፻፶፭

**CONTENT**

**REGULATION No.183 /2024**

**A REGULATION OF BICYCLE SHARING SERVICE AND THE USE OF BICYCLE LINE OF THE ADDIS ABABA CITY**

**Page**……………………………………..……..…..3855

## ደንብ ቁጥር ፻፹፫/፪ሺ፲፮

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብስክሌት መጋራት አገልግሎት እና የብስክሌት መስመር አጠቃቀም ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ የተሽከርካሪ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር ምክንያት የሚያጋጥመውን የትራፊክ እንቅስቃሴ መጨናነቅ ለማቃለል፣ የከባቢ አየር ብክለት ለመቀነስ፣ ከቦታ ወደ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴን ለማቀላጠፍ፣ ብስክሌት በማሽከርከር የአካል ብቃትን ለማዳበር፣ የአእምሮ ዕድገትን ለማጠናከር እና ጤናማ ዜጋ እንዲሆኑ ለማስቻል የሞተር አልባ ትራንስፖርት አገልግሎትን ማስፋፋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

## REGULATION No.183/2024

## A REGULATION OF BICYCLE SHARING SERVICE AND THE USE OF BICYCLE LINE OF THE ADDIS ABABA CITY

**WHWREAS,** it has become necessary to the expansion of transportation without a motor to enable health citizen, to develop a physical competence by driving a bike, to strengthen mental growth to facilitate the movement from place to place, to reduce the pollution of environment, to reduce the risk of the traffic congestion caused by the highly increasing number of the vehicle of the Addis Ababa city;

በከተማ አስተዳደሩ የተከናወነው የኮሪደር ልማት ሥራ ለአጠቃላይ ከተማችን እድገት ገጽታ ግንባታና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ በተጨማሪ የብዙሃን ትራንስፖርት መሰረተ-ልማቶች ችግርን የሚያቃልል እና የትራፊክ ፍሰቱን የሚያሻሻል በመሆኑ የተገነባውን የብስክሌት መስመር በተሟላ ሁኔታ አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሞተር አልባ ትራንስፖርት አገልግሎት ለማስፋፋት የተገነቡትን የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ በማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ወጭ ቆጣቢ፣ ተደራሽ፣ ፍትሀዊና ዘላቂነት ያለው እና የማህብረሰቡን ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፺፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ " የብስክሌት መጋራት አገልግሎት እና የብስክሌት መስመር አጠቃቀም ደንብ ቁጥር ፻፹፫/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪ ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ ወይም ሐረግ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

**WHWREAS,** it has become necessary to establish a procedure to apply the constructed of the bicycle service line to improve the flow of the traffic. In addition to economic benefits, the contribution for mass transport infrastructures embraces a problem and the corridor development done by the city government for the development of our general feature;

**WHWREAS,** it has become necessary to establish a procedure to the bicycle transport service that allows the needs of the community and fair and sustainable, accessible, cost effective, secure and to expand the transportation without a motor to meet their objective;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "A Bicycle Sharing Service and the Use of Bicycle Line of the Addis Ababa City Government Regulation No. 183/2024".

### 2. Definition

Unless the context or phrase requires otherwise in this regulation:

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. "**ቢሮ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

፫. **"የሞተር አልባ ትራንስፖርት"** ማለት የነዳጅ ሃይል ሳይጠቀም ሰውን ወይም ዕቃን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚያገለግል የትራንስፖርት ዓይነት ነው፤

፬. "**ብስክሌት**" ማለት በፔዳል፣ በባትሪ ወይም በሁለቱም የሚንቀሳቀስ ባለሁለት ጎማ ወይም ባለ ሦስት ጎማ ሞተር አልባ ተሽከርካሪ ሲሆን ስኩተርን የሚያካትት ነው፤

፭. "**ስኩተር**" ማለት በኤሌትሪክ ባትሪ የሚንቀሳቀስ ባለሁለት ጎማ ሆኖ ተሳፋሪው ቆሞ የሚነዳው ተሽከርካሪ ነው፤

፮. **"የብስክሌት ጣቢያ"** ማለት የብስክሌት ትራንስፖርት መጋራት አገልግሎት ማቆሚያ ቦታ ነው፤

፯. **"ብስክሌት መጋራት"** ማለት ተጠቃሚዎች ለኦፕሬተሩ የአግልግሎት ክፍያ በመክፈል ብስክሌትን በመተካካት በጋራ ለትራንሰፖርት አገልግሎት የሚጠቀሙበት አሰራር ነው፤

፰. "**የብስክሌት ኪራይ**" በኦፕሬተሩ እና በብስክሌት ተከራይ ሰው መካከል የሚደረግ የኪራይ ስምምነት ነው፤

፱. **"የብስክሌት መስመር"** ማለት ለብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ እንዲውል የተገነባ የጉዞ መስመር ነው፤

1. **"City"** means the Addis Ababa City Government;

2. **"Bureau"** means the Transport Bureau of the Addis Ababa City Government;

3. **"Transportation without Motor "** means the type of transportation that is used to move a person or item from one place to another without using fuel power;

4. **"Bicycle"** means moving by pedal, by battery or both moves and three tires transport without motor including scooter;

5. **"Scooter"** means a two-wheel-headed vehicle that will stand the passenger moving in electric battery;

6. **"Bicycle Stop"** means a bicycle transport sharing service stopping area;

7. "**Sharing Bicycle**" means the procedure by implementing the bicycle by paying users to the operator's service charge commonly using for transportation service;

8. "**Bicycle Rent**" is a rental agreement between the operator and bicycle tenant;

9. **"Bicycle Line"** is a travel line used to be only for bicycle transport service;

፲. **“ኦፕሬተር”** ማለት የብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተመዘገበ እና የሥራ ፈቃድ ያለው የብስክሌት ባለንብረት ነው፤

፲፩.**“ተጠቃሚ”** ማለት ከኦፕሬተር ጋር በኪራይ ያገኘውን ብስክሌት ወይም ስኩተር የሚጠቀም ሰው ሆኖ እንደአግባቡ የግሉን ብስክሌት በብስክሌት መስመሩ ላይ የሚጋልበውን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ያካትታል፤

፲፪.**“የኦፕሬተርነት የሥራ ፈቃድ”** ማለት ቢሮው በብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለሚሰማራ ሰው የሚሰጠው የሥራ ፈቃድ ነው፤

፲፫.**“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬.በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**፫.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማት በተከናወነባቸው አካባቢዎች በተዘረጋ የብስክሌት መስመር ላይ አገልግሎት በሚሰጡ ኦፕሬተሮች እና ዕድሜያቸው ፲፭ ዓመት እና በላይ የሆናቸው ብስክሌት ተጠቃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የብስክሌት አገልግሎት ዓይነት እና የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ</u>**

**፬.<u>የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነት</u>**

የብስክሌት አገልግሎት ዓይነት የሚከተለው ይሆናል፡-

10. **"Operator"** means the owner of a bicycle who has registered and has work license to provide a bicycle transportation service;

11. **"User"** means a person who is used the bicycle or scooter with operator rent according to private bicycle ride on the bicycle line and consists of an adult person;

12. **"Operator's Work License"** means the work license for someone who engages in the bicycle transportation service provided by the Bureau;

13. **"Person"** means any natural or juridical person;

14. In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be Applicable to bicycle line operators and their ages are 15 years and above of bicycle users on a bicycle line service in the city government.

**<u>PART TWO</u>**

**<u>TYPE OF BICYCLE SERVICE AND WORK LICENSE</u>**

**4. <u>Type of Bicycle Transportation Service</u>**

The type of bicycle service will be the following:

፩. ብስክሌቱን የሚያሽከረክረው ሰው በራሱ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ፤

፪. ባለው የዕቃ ማስቀመጫ ቦታ ላይ በመጠቀም እቃዎችንና መልእክቶችን ማመላለስ፡፡

## ፭.ፈቃድ ስለማውጣት

፩.ማንኛውም በኦፕሬተርነት መሰማራት የሚፈልግ ሰው የሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፤

፪.ቢሮው በኦፕሬተርነት ሥራ ላይ የሚሰማራን ማንኛውም ሰው የሚመዘግብበት መዝገብ ያደራጃል፡፡

## ፮.የኦፕሬተርነት የሥራ ፈቃድ መስፈርት

በኦፕሬተርነት ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

፩. ብዛቱ ፫፻ (ሦስት መቶ) እና ከዚያ በላይ የብስክሌት እና/ወይም ከ፩፻ (አንድ መቶ) የማያንስ ስኩተር ለአገልግሎት ማቅረብ የሚችል፤

፪. ደረጃውን የጠበቀ ጂፒኤስ ያለው ወይም የተገጠመለት ብስክሌት ማቅረብ የሚችል፤

፫. የስራ ውል ስምምነት የሚፈርም፤

፬. ሥራውን የሚመራበት ቢሮ ያለው፤

፭. የብስክሌት ኦፕሬሽን፣ የብስክሌት ጥገና ዘርፍ የሥራ ክፍሎች እና ለጥገና የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ያሉት፤

፮. የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጫ ኪት በየብስክሌት ጣቢያ ማዘጋጀት የሚችል፤

1. The rider of the bicycle in itself, and to move from place to place;
2. Taking back and forth items and messages using the container space.

## 5. Issuance of Work License

1. Anyone who wants to engage in operator must be issued a work license;
2. The Bureau will organize a record where anyone who engaged in the operator works.

## 6. Operator Work License Requirement

Anyone who wants to engage in operator should meet the following requirements:

1. Providing the service quantity of 300 (three hundred) and above the bicycle and / or less than 100 (one hundred) scooter;
2. Providing a bicycle which contains the standard of GPS, or fitted with GPS;
3. Who have signed the work agreement;
4. Who have an office of the work;
5. Who have a bicycle operation, bicycle maintenance sectors and of the bicycle maintenance equipment;
6. Primary care kit can set a bicycle station;

፯. ለድርጅቱ ሠራተኞች ደረጃውን የጠበቀ ዩኒፎርም እና የድርጅቱ መታወቂያ ሊያሟላ የሚችል፤
፰. የኢንተለጀንት ትራንስፖርት ሥርዓት መሠረት ያደርገ የጥሪ ማእከል ማዘጋጀት የሚችል፤
፱. የአገልግሎት መስጪያ መተግበሪያ ሶፍት ዌር መጠቀም የሚችል፡፡

## ፯.የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ

፩. ማንኛውም ኦፕሬተር በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲቀርብ የኦፕሬተርነት የሥራ ፍቃድ ይሰጠዋል፤
፪ የሥራ ፈቃዱ የሚያገለግለው ለወጣበት በጀት ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

## ፰.የሥራ ፈቃድ ስለማደስ

፩. ማንኛውም ኦፕሬተር የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ በየዓመቱ ማደስ አለበት፤

፪. የሥራ ፈቃዱ የሚታደስበት ጊዜ በየዓመቱ ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ታህሳስ ፴ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተደነገገው ጊዜ ውጪ የሚቀርብ የሥራ ፈቃድ እድሳት ጥያቄ የሚስተናገደው በቅጣት ሆኖ ከጥር ፩ ቀን እስከ ሰኔ ፴ ድረስ ላለው ጊዜ ከሥራ ፈቃድ ማሳደሻ በተጨማሪ የሥራ ፈቃድ ማሳደሱ ለዘገየበት፡-

ሀ) ለጥር ወር የሥራ ፈቃድ ማሳደሻ ክፍያው ላይ ፴% (ሠላሳ በመቶ)፤

7. Must fulfill the standardized uniform and the ID of the organization for staff of the organization;
8. Set up a call center based on intelligent transport system;
9. Using the service provide application software.

## 7. Work License

1. Any operator provides an operator work license when meet the requirements in accordance with Article 6 of this regulation;
2. The work license will be used only for the fiscal year.

## 8. Renewal of Work License

1. Any operator must renew the work license;
2. The time of the work license will be within the period of July 1 to December 30, each year;
3. Renewal of work license out of the time of Sub Article (2) of this Article, to the time of the January 1 of June 30 the work license in addition for delay has been penalized in the following:
   a) 30% (thirty percent) on the January month work license renewal payment fee;

ለ) ለሚቀጥለው ለእያንዳንዱ ወር የሥራ ፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ ፲% (አሥር በመቶ) ቅጣት ተጨምሮ በቅጣት ያድሳል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ መሰረት እስከ ሰኔ ፴ ያልታደሰ የሥራ ፈቃድ ይሰረዛል፤

፭. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሥራ ፈቃዱን ማሳደስ ያልቻለ መሆኑን በበቂ ማስረጃ ማስረዳት ከተቻለ የተጠቀሰውን የእድሳት እና የቅጣት ክፍያ በመክፈል የሥራ ፈቃዱን ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ባለው ሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የሥራ ፈቃዱን ማደስ ይችላል፤

፮. ማንኛውም ኦፕሬተር የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ ማደስ የሚችለው የሚፈለግበትን ዓመታዊ ግብር መክፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዞ ሲቀርብ ይሆናል፡፡

## ፱. <u>የአገልግሎት ክፍያ</u>

የኦፕሬተርነት ፈቃድ ለማግኘት፣ ለማሳደስ ወይም ለመቀየር የሚከተለውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡-

፩. የኦፕሬተርነት የሥራ ፈቃድ ለማግኘት ብር ፰ ሺህ (ስምንት ሺህ ብር)፤

፪. የኦፕሬተርነት የሥራ ፈቃድ ለማደስ ብር ፭ ሺህ (አምስት ሺህ ብር)፤ ወይም

፫. የጠፋን የኦፕሬተርነት የሥራ ፈቃድ ለመተካት ብር ፬ሺህ (አራት ሺህ ብር)፤

፬. የአገልግሎት ክፍያው በየጊዜው እየተጠና የሚሻሻል ይሆናል፡፡

b) 10% (ten percent) penalties for each month of work licenses renewal payment with a penalty.

4. In accordance with Sub Article (3) of this Article, the work permit did not renewed to July 07 will be cancelled;

5. Despite the provision of Sub Article (4) of this Article, if there is force majeure and has reasoning for adequate proof, the work license will be renewed within three months of the date of renewal and penalty payment;

6. Any operator will be renewed with a proof that it will be renewed by paying the annual tax; he will be when it is confirmed.

## 9. <u>Service Charge</u>

To obtain work license, to renew or to replace it must pay the following service charge:

1. 8000 (eight thousand) Birr for obtaining work license;

2. 5000 (five thousand) Birr to renew operator work license; or

3. 4000 (four thousand) Birr to replace the lost operator work license;

4. The service charge will be regularly studied and amended.

## ፲.የሥራ ፍቃድ ስለመሰረዝ

ቢሮው የኦፐሬተሩን የሥራ ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፡-

፩. ኦፐሬተሩ በዚህ ደንብ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ የሥራ ፈቃዱን ሳያሳድስ ሲቀር፤
፪. ክትትልና ቁጥጥር ሲያደርግ ያገኘውን ጉድለት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማስተካከል ሳይችል ሲቀር ወይም ለማስተካከል ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፤
፫. የኦፐሬተርነቱን ሥራ በራሱ ፈቃድ ሲተው፤
፬. የሥራ ፈቃዱን ያወጣው በተሳሳተ ወይም በተጭበረበረ ማስረጃ ሆኖ ሲገኝና ሲረጋገጥ፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ መብትና ግዴታ

## ፲፩.የኦፐሬተሩ መብት

ማንኛውም ኦፐሬተር የሚከተሉት መብት ይኖሩታል፡-

፩. በዚህ ደንብ የተደነገጉ መስፈርቶችን አሟልቶ የሥራ ፈቃድ የማግኘት፤
፪. ቢሮው የሚያቀርበውን ልዩ ልዩ ድጋፎችን የማግኘት፤
፫. የብስክሌት መጋራት አገልግሎት በጥናት ላይ የተመሰረተ አማራጭ የጉዞ መስመሮችን፣ የታሪፍ ምጣኔዎችን የማቅረብ እና ሲፈቀድ የመጠቀም፤
፬. የብስክሌት ትራንስፖርት መጋራት አገልግሎት ላይ ለመሰማራት ከሚፈልጉ ከሌሎች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር በጥምረት የመስራት፡፡

## 10. Cancellation of Work License

The Bureau may be cancelled the operator’s work license in the following reasons:

1. When the operator is not renewed the work license with in time set by this regulation;
2. The deficiency that received supervision and control, but not to adjust or change in the due time;
3. When the operator is left the work on his own;
4. When it is found in wrong or fraudulent evidence and confirmed by obtaining the operator of the work license.

## PART THREE
## RIGHT AND OBLIGATION

## 11. The Right of the Operator

Any operator will have the following right:

1. Completed the requirements of this rule to obtain the work license:
2. To obtain the different supports that the Bureau offers;
3. Use bicycle sharing service optional travel lines based on the study, to provide tariff rates and use when approved.
4. Working with other individuals or organizations who want a bicycle transport sharing service.

## ፲፪. የኦፕሬተሩ ግዴታ

ማንኛውም ኦፕሬተር የሚከተለው ግዴታ ይኖርበታል፡-

፩. የብስክሌት ወይም ስኩተር መጠን እና ዓይነት ለቢሮው ማቅረብ፤ ሲወሰን ተግባራዊ ማድረግ፤

፪. ቢሮው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት የብስክሌቱ መለያ ቁጥር፣ የኦፕሬተሩን እና የቢሮ የጥሪ ማዕከል የስልክ አድራሻ በብስክሌቱ አካል ላይ መለጠፍ፤

፫. የጥሪ እና የመረጃ ማዕከል የማቋቋም፤

፬. የጂፒኤስ አገልግሎት የመጠቀም፤

፭. የብስክሌት ስምሪትን የመከታተል፤

፮. ቢሮው ባፀደቀው የታሪፍ ምጣኔ መሰረት አገልግሎት መስጠት፤

፯. በሥራ ውል ስምምነት መሰረት አገልግሎት የመስጠት፤

፰. ከብስክሌቱ የአካል ጎን እና ከፍታ መጠን ያልወጣ እስከ ፲ ኪሎ ግራም ድረስ የሚጫነው እቃ እይታን የማይከልል እና ለአደጋ የማያጋልጥ መሆኑን የማረጋገጥ፤

፱. የአገልግሎት ክፍያ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ፤

፲. በምሽት የሚሰማሩ ብስክሌቶች ላይ በጉልህ የሚታይ አንፀባራቂ ምልክቶችን መለጠፍ፤

፲፩.ለሠራተኞቹ መታወቂያ፣ ባጅ እና ዩኒፎርም የማዘጋጀት፤

፲፪.ለብስክሌት ማቆሚያ ተብሎ በተለየ ቦታ ላይ የብስክሌት ማቆሚያ የመስራት፤

፲፫.ፆታን ታሳቢ ያደረገ የብስክሌት ዓይነት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 12. The Obligation of the Operator

Any operator will have the following obligation:

1. Submit the bicycle or scooter quantity and type to the Bureau; apply when it is approved;
2. Posting the bicycle's identity number, the operator and office call center posting on bikes body based on the standard takes it out by the Bureau;
3. Establishing a call and information center;
4. Use a GPS service;
5. Attending a bicycle deployment;
6. Provide a service tariff rates approved by the Bureau;
7. Provide services based on work agreement;
8. Confirms that it does not cover a view and expose the items that are loaded up to 10 kg of the body and levels of bicycle;
9. Make a service charges supported by technology;
10. Posting the signs of clear reflector on bicycles deployed at night;
11. Make a badge and uniforms for staff;
12. Working a bicycle stop in a different place called a bicycle stop;
13. Must provide bicycle type considered on sex.

## ፲፫.የተጠቃሚ መብት

፩. በተፈቀደው የጉዞ መስመር የመጠቀም፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም እድሜያቸው ከ፲፭ ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት በብስክሌት መስመሩ የሚገለገሉት ከወላጆቻቸው ጋር ሲሆኑ ብቻ ይሆናል፤

፫. ከኦፕሬተሩ አገልግሎት የሚያገኝ ተጠቃሚ፡-

ሀ) በሚሰጠው አገልግሎት ላይ መረጃ የመጠየቅና የማግኘት፤

ለ) የሚመቸውን የብስክሌት አይነት የመምረጥ፤

ሐ) የቴክኒክ ችግር ሲገጥም በመተላለፊያ ጣቢያ ላይ ከሚገኘው ብስክሌት በመቀየር ጉዞውን የማጠናቀቅ፤ መብት አለው፡፡

## ፲፬.የተጠቃሚ ግዴታ

፩. ተጨማሪ ሰው አለመጫን፤

፪. የትራፊክ ህግ የማክበር፤

፫. በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ብስክሌቱንና መንገዱን ለትርዒት ያለመጠቀም፤ግዴታ አለባቸው፡፡

## ፲፭.በብስክሌት ላይ ስለሚጫን ዕቃ

በብስክሌቱ ላይ ለዕቃ መጫኛ በተዘጋጀው ቦታ ላይ የሚጫነው ዕቃ ከብስክሌቱ የአካል ጎን እና ከፍታ መጠን ያልወጣ እስከ ፲ ኪሎ ግራም ድረስ ክብደት ያለው እይታን የማይከለክል እና ለአደጋ የማያጋልጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 13. User Right

1. Using the permitted travel line;
2. In spite of Sub Article (1) of this Article, children under 15 years of age will be only served with their parents;
3. A user from the operator service:
   a) Receiving and obtain information on services provided;
   b) To choose a bicycle type which suits to him;
   c) When it is fired a technical problem, has the right to move and change the bicycle on the transmission site.

## 14. User Obligation

1. Do not load anymore;
2. Respecting traffic law;
3. Unless otherwise permitted in special situation, have the duty not use the bicycle and the way for show.

## 15. The Loaded Item

The loaded item in the place that is set to a parcel on the bicycle do not above body part have up to 10 kilo gram and level must not cover the view and it should be not to danger.

## ክፍል አራት

## ለአገልግሎት ስለሚቀርብ ብስክሌት፣ ማቆሚያ ቦታ እና የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

**፲፮. ለአገልግሎት የሚቀርብ ብስክሌት**

ማንኛውም ኦፕሬተር ለአገልግሎት የሚያቀርበው፡-

፩.ብስክሌቱ የተመረተበት ዘመን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ፤

፪. የብስክሌቱ ዓይነት ሃይብሪድ፣ በኤሌክትሪክ ባትሪ ወይም በማንዋል የሚሰራ፤

፫. የብስክሌት የቀለም ዓይነት አንድ ወጥ ሆኖ ከሌላው ኦፕሬተር ጋር የማይመሳሰል፤ መሆን አለበት፡፡

**፲፯. ስለብስክሌት ማቆሚያ ቦታ**

ማንኛውም ኦፕሬተር፡-

፩. አገልግሎት የሚሰጥባቸው ብስክሌቶች በየደረጃቸውና ዓይነታቸው ተስተካክለው ለዕይታ ማራኪ ሆነው የሚቆሙበት አመቺ የብስክሌት ማቆሚያ ቦታ ማዘጋጀት አለበት፤

፪. የብስክሌቶቹ ማቆሚያ ቀለም ብስክሌቶቹ ከሚቆሙት አካባቢ ቀለም ጋር ተተስማሚ ማድረግ አለበት፤

፫. የብስክሌት ማቆሚያ ቦታውን ቢሮው በሚያወጣው ወይም እንዲወጣ በሚያደርገው ስታንዳርድ መሰረት ያዘጋጃል፡፡

**፲፰. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት**

ቢሮው አግባብነት ባለው ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

## PART FOUR

## A BICYCLE FOR SERVICE, THE STOP PLACE AND DUTY AND RESPONSIBILITY OF THE BUREAU

**16. A Bicycle for Service**

Any operator offers to the service:

1. The time of the produced period of the bicycle is not more than two years;
2. The bicycle type of hybrid, electric battery or working by manual;
3. A bicycle color type of color is one dish must be not the same with the other operator.

**17. A Bicycle Stop**

Any operator:

1. The convenient bicycle stopping place for service bicyclists in their levels and their types;
2. The bicycles stops should be suitable with the color of the bikes;
3. Sets according to the standard that the bicycle stop is issue or to issue by the Bureau.

**18. Duty and Responsibility of the Bureau**

As expected powers and responsibilities given by relevant law, the Bureau have the following detailed duty and responsibility:

፩. የኦፕሬተርነት የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤
፪. ከኦፕሬተሮች ጋር በኔትዎርክ በመተሳሰር የጂፒኤስ፣ የሬዲዮ አገልግሎቶችን ይዘረጋል፣ አሰራሩን ይከታተላል፤
፫. ለኦፕሬተሮች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
፬. ኦፕሬተሩ የአገልግሎት መስጫ የታሪፍ ዋጋ ዝርዝር ሲያቀርብ ያፀድቃል ወይም የራሱን ታሪፍ ያወጣል፤
፭. የብስክሌት መጋራት አገልግሎት በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውል ለህብረተሰቡ ያስተዋውቃል፤ያበረታታል፤
፮. የብስክሌት ጉዞ መስመር መነሻ፣ መተላለፊያ እና መድረሻ ቦታዎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ይለያል፣ ይወስናል፤
፯. ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያን ይሰበስባል፤
፰. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፤
፱. ይህን ደንብ የሚተላለፉ ወይም ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ኦፕሬተሮች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ክልከላ እና አስተዳደራዊ እርምጃ

### ፲፱. ክልከላ

፩ ማንኛውም ኦፕሬተር፡-

ሀ) ጂፒኤስ ሳይገጠም ወይም በማይሰራ ጂፒኤስ አገልግሎት መስጠት፤

ለ) ከፀደቀው ታሪፍ በላይ ማስከፈል፤

ሐ) በብስክሌቱ ላይ ተጨማሪ ሌላ አካል መግጠም፤

1. Provides operator work license, renews, cancel;
2. Networking with operators providing the GPS, radio services and follow the procedure;
3. Provides necessary support to operators;
4. Approves the operator's detailed tariff rate of service or issue its own tariffs;
5. Introduces and promotes bicycle sharing service to be used widely to the society;
6. Determine the bicycle trip line starting passage and destination places based on the study;
7. Collects a charge for the service provided;
8. Shall be assigned to transportation inspectors to enforce the provisions of this regulation;
9. It will take or makes it be taken administrative action on operators who do not have responsibilities or violates this regulation.

## PART FIVE

## PROHIBITION AND ADMINISTRATIVE ACTION

### 19. Prohibition

1. Any Operator:

a. Provide service without fitting GPS or with not worked GPS;

b. Charge more than approved tariffs;

c. Fitting other additional body on the bicycle;

መ) የኦፕሬተርነት ሥራ ፈቃድ ሳይኖር ወይም ሳያሳድስ አገልግሎት መስጠት፤

ሠ) በደንቡ መሠረት ያልተፈቀደ የብስክሌት ቀለም ቀብቶ አገልግሎት መስጠት፤

ረ) ሌላ ኦፕሬተር የሚጠቀምበትን መለያዎች መጠቀም፤

ሰ) የኦፕሬተርነት ፈቃድ ከተሰጠበት አገልግሎት እና የጉዞ መስመር ውጪ መስራት፤

፪ <u>ማንኛውም ተጠቃሚ፡-</u>

ሀ) ከተፈቀደው የመጫን አቅም በላይ መጫን፤

ለ) ብስክሌት እየነዱ መመገብ፣ መጠጣት፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠቀም፤ ማጨስ፤

ሐ) ከኦፕረተሩ የተከራየ ተጠቃሚ ከስምምነት መስመር ውጪ መጋለብ፤

መ) የሌሎች ብስክሌት መንገድ ተጠቃሚዎችን እንቀስቃሴ ማወክና ለአደጋ በሚጋብዝ መልኩ ብስክሌት መጋለብ፤

ሠ) የብስክሌቱን መሪ ለቀ ወይም የብስክሌቱን መሪ በእግር ይዞ መንዳት፤

ረ) በእንቅስቃሴ ወቅት የብስክሌት መስመሩን ለሚያቋርጡ ተሽከርካሪዎች እና ለእግረኛ ቅድሚያ ያለመስጠት፤

ሰ) አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በብስክሌቱ ወይም በብስክሌት መስመሩ ላይ ከብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ውጪ ለትርዒት መጠቀም፡፡

d. Provide service without operator work license or providing service without renewal;

e. Provide service by unauthorized bicycle color in accordance with the regulation;

f. Use of identifications used by another operator;

g. Work out of operator service and travel line.

**2. <u>Any user:</u>**

a. loaded over the permitted capacity of the load;

b. Feeding, drinking, using mobile phone, smoking cigarette while riding a bicycle;

c. The rented user from the operator uses outside of agreed line;

d. Disturbing the movement of other bicycle riders and a bicycle in a way that is in danger;

e. Left the bicycle leader or riding the bicycle’s leader by foot;

f. No giving priority to vehicles that cross the bicycle line and to the pedestrian;

g. Using the show outside of the bicycle transport service without permission to the appropriate body.

## ፳. አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ

፩.በወንጀል ሕግ እና በሌሎች ሕጎች የተደነገገው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአግባቡ ቢሮው ወይም የከተማው አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ይህንን ደንብ በተላለፈ ማንኛውም ሰው ላይ፡-

ሀ) እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የመከላከል፣ የማስቆም እና የሥራ ፈቃድ እንዲሰረዝ የማድረግ፣

ለ) በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ መሰረት አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፤

፪. በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈያ ዘዴ በሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣቱን ገቢ በማድረግ ቅጣቱን መፈጸም አለበት፤

፩. የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት መቀጫ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤

## 20. Taking Administrative Action

1. As the penalty regarded by criminal law and other laws the Bureau or the Traffic Management Authority on anyone who has passed this regulation:

   a) As the result of the fault, to defend, to stop and cancelled the operating work license;

   b) Shall be generated by administrative fine in accordance with the attached table.

2. Shall be generated by administrative fine in accordance with the attached Anyone who was administrative fine according to this regulation, in the case of the administrative fine by holding an announcement paper or pay immediately through electronics payment method within three consecutive business days in the area where the presence of fault at the branch office of Traffic Management Authority in the area;

   1. It assumed that if not a permission to receive a penalty announcement, it will be enforced in accordance with to Sub Article (4) of this Article;

   2. A person who does not paid administrative fine will pay twice as required by Sub Article (3) of this Article;

፫. የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ማንኛውም ሰው አስተዳደራዊ ቅጣቱን ለማስፈጸም ለከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ይልካል፡፡

**፳፩. <u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ</u>**

፩. ቅሬታ ወይም አቤቱታ ያለው ኦፕሬተር ወይም ተጠቃሚ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ወይም አቤቱታውን በራሱ ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት በፅሁፍ ወይም ማንኛውንም ቴክኖሎጂ በመጠቀም በየደረጃው ለሚገኝ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ ያስነሳው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤

፪. ቅሬታው የደረሰው የቢሮ ወይም ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታው በደረሰው አምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለበላይ ኃላፊው ማቅረብ አለበት፤

፫. የውሳኔ ሀሳብ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤ በቢሮ ደረጃ ወይም የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፤

፬. በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፳፪. <u>የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፍ</u>**

ማንኛውም የብስክሌት ትራንስፖርት መጋራት አገልግሎት የሚሰጠው ኦፕሬተሩ በሚያቀርበው አገልግሎት ዓይነት እና ሌሎች ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በጥናት ላይ ተመስርቶ ለቢሮው በሚያቀርበው እና በቢሮው በሚጸድቅ ታሪፍ መሰረት ይሆናል፡፡

3. The Traffic Management Authority shall send administrative fine to Justice Bureau of Addis Ababa City Government to implement the administrative fine in accordance with to Sub Article (4) of this Article.

**21. <u>Grievance Procedure</u>**

1. Operator or user or any person who has complained can provide his complain with in person or his legal representative with written statement or any other technology to the complaint committee within three consecutive business days from the date of payment;

2. The complaint Bureau or the Traffic Management Authority and the complainant committee must prepare the recommendation and provide to the Head within five consecutive business days of the complaint;

3. The recommended head must be informed in writing in five business days; the decision given by the Bureau level or Code Enforced Authority will be final;

4. Anyone who is disappointed by the final decision can provide the complaint with the court of jurisdiction.

## <u>PART SIX</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**22. <u>Bicycle Transport Service Tariff</u>**

Any bicycle transport sharing service by the operator will be based on the type of study and situations and approved tariff by the Bureau provided by the operator.

**፳፫.** **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ይህንን ደንብ በመፈጸምና በማስፈጸም ሂደት ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፬.** **<u>ተፈጻሚነት ስሌላቸው ህጎች</u>**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማ ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፭.** **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ጥር ፳፱ ቀን/፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**23. <u>Duty to Cooperate</u>**

Everyone has obliged to cooperate with in the process of executing and implementing this regulation.

**24. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any regulation, directive or customary practice of the City Cabinet does not apply to issues covered by this Regulation.

**25. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of this 6th day of Feb, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 6th day of Feb 2024.**

**Adanech Abiebie Desa**

**Mayor of Addis Ababa City**

## ሠንጠረዥ

## አስተዳዳራዊ የገንዘብ ቅጣት

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የቅጣት መጠን በገንዘብ |
|---|---|---|
| 1 | **ማንኛውም ኦፐሬተር፡-** | |
| | ሀ) ጂፒኤስ ሳይገጠም ወይም በማይሰራ ጂፒኤስ አገልግሎት መስጠት፤ | ፫ሺ. ብር |
| | ለ) ከፀደቀው ታሪፍ በላይ ማስከፈል፤ | ፫ሺ.፬፻ ብር |
| | ሐ) በብስክሌቱ ላይ ተጨማሪ ሌላ አካል መግጠም፤ | ፭ሺ. ብር |
| | መ) የኦፐሬተርነት ሥራ ፈቃድ ሳይኖር ወይም ሳያሳድስ አገልግሎት መስጠት፤ | ፲ሺ. ብር |
| | ሠ)በደንቡ መሠረት ያልተፈቀደ የብስክሌት ቀለም ቀብቶ አገልግሎት መስጠት፤ | ፲ሺ. ብር |
| | ረ)ሌላ ኦፐሬተር የሚጠቀምበትን መለያዎች መጠቀም፤ | ፲ሺ. ብር |
| | ሰ)የኦፐሬተርነት ፈቃድ ከተሰጠበት አገልግሎትና የጉዞ መስመር ውጪ መሰማራት፤ | ፲ሺ. ብር |
| 2 | **ማንኛውም ተጠቃሚ፡-** | |
| | ሀ) ከተፈቀደው የመጫን አቅም በላይ መጫን፤ | ፮፻ ብር |
| | ለ) ብስክሌት እየነዱ መመገብ፣ መጠጣት፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠቀም፣ ማጨስ፤ | ፭፻ ብር |
| | ሐ)ከኦፐሬተሩ የተከራየ ተጠቃሚ ከስምምነት መስመር ውጪ መጋለብ፤ | ፩ሺ.፭፻ ብር |
| | መ) የሌሎች ብስክሌት መንገድ ተጠቃሚዎችን እንቅስቃሴ ማወክና ለአደጋ በሚጋብዝ መልኩ ብስክሌት መጋለብ ፤ | ፭፻ ብር |
| | ሠ) የብስክሌቱን መሪ ለቆ ወይም የብስክሌቱን መሪ በእግር ይዞ መንዳት፤ | ፭፻ ብር |
| | ረ)በእንቅስቃሴ ወቅት የብስክሌት መስመሩን ለሚያቋርጡ ተሽከርካሪዎች፣ እና ለእግረኛ ቅድሚያ ያለመስጠት፤ | ፮፻ ብር |
| | ሰ) አግባብ ያለው አካል ሳይፈቀድ በብስክሌቱ ወይም በብስክሌት መስመሩ ላይ ከብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ውጪ ለትርዒት መጠቀም፡፡ | ፩ሺ. ብር |

## Table

## Administrative Fine

| No. | Type of Fault | Amount of Fine in money |
|---|---|---|
| 1 | **Any Operator** | |
| | a) Provide service without fitting GPS or with not worked GPS; | 3,000.00 Birr |
| | b) Charge more than approved tariffs; | 3,400.00 Birr |
| | c) Fitting other additional body on the bicycle; | 5,000.00 Birr |
| | d) Provide service without operator work license or providing service without renewal; | 10,000.00 Birr |
| | e) Provide service by unauthorized bicycle color in accordance with the regulation; | 10,000.00 Birr |
| | f) Use of other identifications used by another operator; | 10,000.00 Birr |
| | g) Work out of operator service and travel line. | 10,000.00 Birr |
| 2 | **Any User** | |
| | a) loaded over the permitted capacity of the load; | 600.00 Birr |
| | b) Feeding, drinking, using mobile phone, smoking cigarette while riding a bike; | 500.00 Birr |
| | c) The rented user from the operator uses outside of agreed line; | 1500.00 Birr |
| | d) Disturbing the movement of other bicycle riders and a bicycle in a way that is in danger | 500.00 Birr |
| | e) Left the bicycle leader or riding the bicycle's leader by foot; | 500.00 Birr |
| | f) No giving priority to vehicles that cross the bicycle line and to the pedestrian; | 600.00 Birr |
| | g) Using the show outside of the bicycle transport service without permission to the appropriate body. | 1000.00 Birr |